በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 216512

ሀምሌ5 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ መብርሀቱ ተጫነ -ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ሀና ተስፋዬ -ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ ትርንጎ በነበሩ -አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 90211 በቀን 20/07/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 270299 በቀን 09/02/2014 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ስለጠየቁ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው አመልካች ባቀረቡት ክስ ሲሆን የአሁን 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡

ከሳሽ በቀን 04/10/2010 ዓ.ም ለስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ከሳሽና ተከሳሽ መስከረም 01 ቀን 1999 ዓ.ም በክብር መዝገብ ሹም ፊት ትዳር መስርተን የካቲት 17 ቀን 2002

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ዓ.ም ጋብቻው በፍቺ ፈርሶ ንብረት ተካፍለን እስከ ሰኔ 23 ቀን 2004 ዓ.ም ተለያይተን ኖረናል፡፡ ነገር ግን በድጋሚ ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ.ም ጋብቻችንን አድሰን እስከ 2010 ዓ.ም ታህሳስ ወር መጀመሪያ በትዳር ኖረናል፡፡ አብረን በትዳር በቆየንበት ግዜ ንብረት በጋራ አፍርተናል፡፡ ይሁንና ተከሳሽ ካንተ ጋር ያለኝ ጋብቻ የፈረሰ ነው ቤቴን ለቀህ ውጣ በማለት ታህሳስ መጀመሪያ 2010 ዓ.ም ከቤት አስወጥታኝ በጋራ ያፈራናቸውን ንብረቶች ሳታካፍለኝ በእጇ ይዛ ችግር ላይ የምገኝና ለልጃችን ስል ለመስማማትም ጠይቄ ፈቃደኛ ባለመሆኗ ሰኔ 24/2004 ዓ.ም በእርቅ አድሰንና ተስማምተን የኖርንበት ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ እና በጋብቻ ወቅት ያፈራናቸውን ንብረቶች የጋራ በመሆናቸው ተከሳሽ ድርሻዬን እንድታካፍለኝ በማለት በዝርዝር ጠይቀዋል፡፡ ይህ የሚታለፍ ከሆነና የሚፈርስ ጋብቻ የለም ከተባለም በሽማግሌ ታርቀን ከሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ከአምስት አመት በላይ እንደ ባልና ሚስትነት የቆየን በመሆኑ የንብረት ድርሻየን እኩል እንድካፈል በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽም በሰጡት መልስ በመካከላችን ህዳር 01/1999 ዓ.ም በክብር መዝገብ ሹም ፊት የፈጸምነው ጋብቻ የካቲት 17 ቀን 2002 ዓ.ም በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 75422 የፈረሰ ሲሆን የጋራ ንብረቶችንም ተካፍለን ከተለያየን በኋላ የተፈጸመ ጋብቻ የለም፡፡ ጋብቻችንን ለማደስ ያደረግነውም የእርቅ ስምምነት የለም፡፡ ፍቺ ከፈጸምን በኋላ እንደ ባልና ሚስት አብረን አልኖርንም፡፡ ስለዚህ ከሳሽ ያቀረበው የፍቺ ጥያቄ ውድቅ ተደርጎ ጋብቻው በፍቺ ከፈረሰ በኋላ በመካከላችን በተፈጠረ ወንድማዊ ግንኙነት በጋራ የወለድናትን ልጅ አልፎ አልፎ ለመጎብኘት ከሚመጣ በስተቀር እንደ ባልና ሚስት አብረን አልኖርንም፡፡ ተከሳሽ የፍቺ ምስክርነት ወረቀት ሳወጣ ከሳሽ አ/ክ/ከተማ ወረዳ 10 ወሳኝ ኩነቶች ቀርቦ የፍቺ ምስክር ወረቀት ቢሰጠኝ እንደማይቃወም ገልጾ በቀን 05/07/2009 ዓ.ም የፍቺና ያላገባች ምስክር ወረቀት ተሰጥቶኛል፡፡ ይህም በከሳሽና ተከሳሽ መካከል ጋብቻ ስላለመኖሩ ግምት ሊያስወስድ የሚችል ግንኙነት የሌለን ስለመሆኑና እንደ ባልና ሚስት ስላለመኖራችን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ከከሳሽ ጋር ባለን ወንድማዊ ግንኙነት ከቤት ሽያጭ ጋር በተያያዘ ልምድ ስላለው ከሚረዳኝ በቀር የባልና ሚስት ግንኙነት የለንም፡፡ ንብረትን በተመለከተም የዘረዘራቸው ንብረቶች በፍቺ ከተለያየን በኋላ ያፈራኋቸው የግል ንብረቶቼ ናቸው፡፡ በመሆኑም የከሳሽ ጥያቄ ውድቅ እንዲደረግና ያቀረባቸው ንብረቶችም የተከሳሽ የግል ንብረቶች ናቸው ተብሎ እንዲወሰን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጣ/ገብ (የአሁን 2ኛ ተጠሪ) ወደ ክርክሩ ገብተው ከሳሽ ከጠየቃቸው ንብረቶች መካከል በኦሮሚያ ክልል ወልመራ ወረዳ 1133 ካ/ሜ ላይ ያረፈው የዶሮ እርባታ ድርጅት የተገዛው በቀን 05/01/2003 ዓ.ም ሲሆን ግዥው የተከናወነው በተከሳሽ ስም ቢሆንም በራሴ ገንዘብ የተገዛ የግል

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ንብረቴ በመሆኑ የከሳሽ ክስ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ከሳሽ ለጣ/ገብ አቤቱታ በሰጡት መልስ የተጠቀሰውን ቤትና ቦታ የገዛነው ከሳሽና ተከሳሽ ስንሆን የገዛነውም በቀን 05/01/2005 ዓ.ም ነው፤ የቤቱንም ዋጋ የከፈልኩት ከሳሽ ነኝ፤ ውሉ ሲጻፍ የቀን ስህተት ስለነበር ጣ/ገብ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም በ2003 ዓ.ም ከተከሳሽ ጋር አዋጥቼ ገዛሁ የሚሉት ሀሰት ነው፤ ጣ/ገብ ዶሮ እርባታው ድርጅት ውስጥ እንድትኖር ያደረግነው ከሳሽና ተከሳሽ ተስማምተን ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተከሳሽ በበኩላቸው የጣ/ገብን አቤቱታ በመደገፍ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃውን ከመረመረ በኃላ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ አመልካችና ተጠሪ በ1999 ዓ.ም ጋብቻ ፈፅመው በ2002 ዓ.ም ፍቺ መፈፀማቸው አልተካካዱም፤ የአመልካች ምስክሮች አመልካችና ተጠሪ ሽማግሌዎችና የሁለቱም የቅርብ ዘመዶች በተገኙበት ሰኔ 24/2004 ዓ.ም እርቅ ፈፅመው አብረው ሲኖሩ እናውቃለን ያሉ ሲሆን ተከሳሽ ምስክሮችና ያላገባች ምስክር ወረቀት እንዲሁም ከሳሽ በፖሊስ ወንጀል ምርመራ ቀርቦ የቤተሰብ አቋም ሲጠየቅ አግብቼ የፈታሁ በማለት የሰጠውን ቃል ሁሉ በሰነድ ማስረጃነት አቅርበዋል፡፡ በዚህም መሰረት ከሳሽና ተከሳሽ በ2009 ዓ.ም በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 15 ቀርበው የፍቺ ሰርተፍኬት እንዲሁም ያላገባ ምስክር ወረቀት ማውጣታቸው ፤ ከሳሽ በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል ምርመራ ቢሮ ቀርበው የቤተሰብ አቋም የፈታ በማለት የሰጡት ቃል፤ ተከሳሽ ቤትና ቦታ በምትገዛባቸው ውሎች ውስጥ ከሳሽ ምስክር ከመሆን ያለፈ ሚና የሌለው መሆኑና በኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 15 የሚገኘውን ቤት ተከሳሽ ስትገዛ የሊዝ ባለይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላይ የተጋሪ ስም ባዶ መሆን፤ ከሳሽ ያቀረባቸው ፎቶዎች ከሳሽና ተከሳሽ ከአዲስ አበባ ውጭ በጎንደር፣ መቀሌና አክሱም አካባቢ አብረው የተንዙ መሆናቸውን ከማሳየት ባለፈ ከሳሽ እንደሚሉት የትዳር ሁኔታ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባልና ሚስት ስለመኖራቸው የሚያረጋግጡት ነገር የሌለ ሲሆን የቪድዮ ማስረጃዎችም የከሳሽንና ተከሳሽን ጋብቻ ሳይሆን የሌሎች ሶስተኛ ወገኖች የመልስ ስነ ስርአት የሚያሳዩ በመሆናቸውና ምንም እንኳ የከሳሽ ምስክሮች ግራቀኙ ሲታረቁ አይተናል ቢሉም የከሳሽና ተከሳሽ አኗኗር ሁኔታና ከሳሽ በተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች እንዲሁም ጋብቻና ፍቺ ለማስፈጸም ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ቀርቦ ጋብቻን በፍቺ ፈርሷል የፍቺ ምስክር ወረቀት ይሰጠን ብሎ መጠየቁ እና ሰርተፍኬት እንዲወጣ ማድረጉ ሲታይ በከሳሽና ተከሳሽ መካከል ቀድሞ የነበረው ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ በድጋሚ እርቅ የቀጠለ ጋብቻም ሆነ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት የለም፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኙ ሊከፋፈሉት የሚገባ ንብረት የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

*ማ ሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ውሳኔው ጸንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች በቀን 13/03/2014 ዓ/ም ባቀረቡት ማመልከቻ ተፈፀመ የሚሉትን ስህተት በመዘርዘር የስር ፍርድ ቤት አመልካችን ማስረጃዎች በተለያየ ምክንያት ሳይቀበል መቅረቱ እንዲሁም የስር ፍ/ቤት የያዘውን ጭብጥ ለመመርመር ማስረጃ ሲመዝን መሰረታዊ የማስረጃ አመዛዘን መርሆችን በመጣስ ውሳኔ መስጠቱን በመጥቀስ ውሳኔው እንዲሻርና አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያፈራቸውን የጋራ ንብረት እኩል እንዲካፈሉ ተብሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርመሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እምዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በቀን 05/05/2014 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ የስር ክርክራቸውን አጠናክረው አመልካች ያቀረበው ቅሬታ ከማስረጃ ምዘና ጋር እና የፍሬ ነገር ክርክር ላይ ያተኮረ ስለሆነ ቅሬታው ውድቅ እንዲደረግ እና የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ አግባብና ህግን መሰረት ያደረገ በመሆኑ እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው በቀን 09/06/2014 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ ቅሬታው አይመለከተኝም በሚል ከክርክሩ ውጭ እንድደረግ ብለዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

በበኩላችን እንደመረመርነው አመልካችና 1ኛ ተጠሪን ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ ያለያየውና ምላሽ ማግኘት የሚገባው ጭብጥ በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኂላ ሰኔ 24/2004 ዓ.ም ሽማግሌዎችና የቅርብ ቤተሰቦች በተገኙበት በመካከላቸው በድጋሚ ጋብቻ ተፈጥሯል? ወይንስ አልተፈጠረም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ የሕግ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካችና 1ኛ ተጠሪ መስከረም 01 ቀን 1999 ዓ.ም በክብር መዝገብ ሹም ፊት ትዳር መስርተው የካቲት 17 ቀን 2002 ዓ.ም ጋብቻው በፍቺ የፈረሰ መሆኑን ግራ ቀኙ አልተካካዱበትም፡፡ በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኂላ ተመልሰው ታርቀው አብረው መኖር እንደጀመሩና ቤት እየቀየሩ በመኖር ልጅም መውለዳቸው በፌዴራል የመ/ደረጃ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ በአመልካች በኩላ በቀረቡ ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ የአመልካች አንደኛ፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ምስክሮች ከሳሽና ተከሳሽ ከ2004 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ አብረው መኖራቸውን፤ አብረው

መኖር የቀጠሉት ሰኔ 24/2004 ዓ.ም ሽማግሌዎችና የቅርብ ቤተሰቦች በተገኙበት በድጋሚ የጋብቻ ውል ስምምነት እና እርቅ አድርገው መሆኑን፤ እርቁም የተደረገው አዲስ ሰፈር ኮንደሚኒየም ቤት ውስጥ መሆኑን፤ ከዚህ ቤት ውስጥ አብረው እየኖሩ ሳለ ዊንጌት አካባቢ ቤት ገዝተው መግባታቸውን፤ በዚህ ቤት እያሉም አንድ ልጅ ወልደዋል በማለት አስረድተዋል፡፡ 4ኛ-6ኛ ምስክሮችም ባልና ሚስት ሆነው ቤትና የዶሮ እርባታውን የተመለከተ ውል ሲያደርጉ እንደሚያውቁ አስረድተዋል፡፡ የተከሳሽ ምስክሮች በበኩላቸው ከከሳሽ ጋር ፍቺ ከፈፀሙ በኃላ ከእናቷ ጋር ትኖር እንደነበር፤ ቤቱንም የገዛችው አባቷ አሜሪካ ስለሚኖር እረድቷት መሆኑን፤ ልጅ የፀነሰችለትም ከጋብቻ ውጪ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኝ ማስረጃ ከፍሲል በተጠቀሰው መልኩ ቢቀርብለትም ይህ ወደጎን በማለት ከፍሲል በተጠቀሰው መልኩ በተለያዩ አካላት ተጻፉ የተባሉ ማስረጃዎች ላይ ተመርኩዞ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

እንደሚታወቀው በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 94 መሠረት ጋብቻ መኖሩን ማስረዳት የሚቻለው በጋብቻ የምስክር ወረቀት መሆኑ የተደነገገ ሲሆን የምስክር ወረቀቱ በሌለ ጊዜ የትዳር ሁኔታ መኖርን በማስረዳት ጋብቻ እንዳለ ማረጋገጥ እንደሚቻል ከሕጉ አንቀጽ 96 እና 97 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህም ሌላ በአንድ ወቅት በጋብቻ የኖሩና የተፋቱ ባልና ሚስት በሚታረቁበት ጊዜ በድጋሚ ጋብቻ መፈጸም የሚገባቸው ስለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ ላይ በግልጽ አልተመለከተም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 23021 በተመሳሳይ ጉዳይ በሰጠው ትርጉም ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኃላ የቀድሞ ተጋቢዎች እንደገና አብሮ መኖር የትዳር ሁኔታ መኖሩን የሚያስገነዝብ ከሆነ ጋብቻ መፈፀሙን የህግ ግምት መውሰድ የሚቻል ስለመሆኑ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ተፋተው እንደገና በሽማግሌዎችና በቤተሰቦቻቸው ፊት ዕርቅ አድርገው አብረው እንደኖሩ በአመልካች ምስክሮች የተነገረው ሲታይ የቀደመ ትዳራቸውን በመቀጠል እራሳቸውን እንደ ባልና ሚስት እንደሚቆጥሩና ቤተሰቦቻቸውና ኀብረተሰቡም ባልና ሚስት ናቸው በማለት የተቀበላቸው መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 96 መሠረት በመካከላቸው የትዳር ሁኔታ መኖሩን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመካከላቸው የትዳር ሁኔታ መኖሩ በዚህ መልኩ ከተረጋገጠ ደግሞ ጋብቻ መፈጸሙ በቤተሰብ ህጉ በአንቀጽ 97/1/ መሠረት ግምት መውሰድ የሚቻል በመሆኑ ይህንን የሕግ ግምት 1ኛ ተጠሪ ማፍረስ የሚቻላቸው በህጉ አንቀጽ 97/2/ መሠረት ጠንካራ እና አስተማማኝ ማስረጃ በማቅረብ ነው፡፡

*ማ ሳታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ምንም እንኳ የከሳሽ ምስክሮች ግራቀኙ ሲታረቁ አይተናል ቢሉም በተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች እንዲሁም ጋብቻና ፍቺ ለማስፈጸም ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ከሳሽ ቀርቦ ጋብቻን በፍቺ ፈርሷል የፍቺ ምስክር ወረቀት ይሰጥ ብሎ መጠየቁ እና ሰርተፍኬት እንዲወጣ ማድረጉና ተያያዥ ማስረጃዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም የተጠቀሱት ማስረጃዎች ከፍሲል የተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ እንደሚጠይቀው የህግ ግምቱን ለማፍረስ አስተማማኝ ማስረጃ ነው የሚባል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 90211 በቀን 20/07/2013 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 270299 በቀን 09/02/2014 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካች አቶ መብርሀቱ ተጫነ እና በ1ኛ ተጠሪ ወ/ሮ ሀና ተስፋዬ መካከል የትዳር ሁኔታ መኖሩ ስለተረጋገጠ ባልና ሚስት ናቸው ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የፍቺ እና የንብረት ክርክሩን ተመልክቶ ተገቢውን ህገዊ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

*ማ ሳታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም